# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ—ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 17
ADDIS ABABA - 8th Decem., 1998


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩፻፵/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
ለእርሻ ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፱፻፲፫


## CONTENTS


Proclamation No. 140/1998
International Development Association Credit Agreement for partly financing the Agricultural Research and Training Project Ratification Proclamation ...................... Page 913


### አዋጅ ቁጥር ፩፻፵/፲፱፻፺፩
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለእርሻ ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር ፵፬ሚሊዮን፭፻ሺህ (አርባ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስ ገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ኦገስት ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆ ናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራ ሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለእርሻ ምርምርና ሥልጠና ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፵/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 140/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 44,500,000 (forty four million five hundred thousand Special Drawing Rights) for partly financing the Agricultural Research and Training Project, was signed in Washington DC, on the 7th day of August, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 8th day of December 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Partly Financing the Agricultural Research and Training project Ratification Proclamation No. 140/1998."


ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. አገስት ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፺፪ የብድር ስምምነት ነው ።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር ፵፬ሚሊዮን፭፻ሺህ (አርባ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement NO. 3092 signed in Washington DC, on the 7th day of August, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 44,500,000 (forty four million five hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of December, 1998.

Done at Addis Ababa, this 8th day of December, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE